በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት የተመደበለትን የመደበኛ ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡
የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኢንስቲትዩቱ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡ ኦዲታችን ፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል፡፡

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ኢንስቲትዩቱ ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

1. ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር ልዩ ልዩ ውል ፈጽሞ ድርድቶቹ በውሉ መሠረት ባለመፈጸማቸው ሊሰበስብ የሚገባ የጉዳት ካሣ በድምሩ ብር 1,227,710.41 ያልሰበሰበ መሆኑ፣
2. ብር 8,214,759.93 ከትምህርት ክፍያ፣ የጨረታ ማስያዣ፣ ለፈተና መፈተኛ፣ ለቅጣትና ከሌሎች የተሰበሰበ ገቢ ኢንስቲትዩቱ በሂሳብ መደብ መሰረት የሙያና የትምህርት ተቋም የሚሰበሰብ ገቢ (ሂሳብ መደብ 1443) እና ከልዩ ልዩ የተሰበሰበ ገቢ ሂሳብ (መደብ 1489) ተለይተው መመዝገብ ሲገባው፣ ገቢው በልዩ ልዩ የተሰበሰበ ገቢ ተብሎ በጥቅል ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ፣
3. በድምሩ ብር 3,320,267.45 የወጪ ሂሳብ አገልግሎቱን ባገኘበት በ2008 በጀት ዓመት መያዝና መመዝገብ ሲገባው በ2009 በጀት ዓመት የተመዘገበ መሆኑ፣
4. ብር 20,426,911.53 በተገቢው የሂሳብ መደብ ሳይመዘገቡ የተገኙ መሆኑ፣

5. ተጨማሪ ውል ሳይገባ ወይም የተገባበት ሰነድ ሳይቀርብ ከመጀመሪያው ውል በላይ ብር 2,239,585.36 ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፣
6. ብር 10,573.00 የተሰረዘ የወጪ ቫውቸር በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (TR) የተመዘገበ መሆኑ፣
7. ኢንስቲትዩቱ የሚጠቀምባቸው የመደበኛ ስልክና የኢንተርኔት ክፍያ ዝርዝር ክፍያው ሳይቀርብ በጥቅል ብር 919,897.99 ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፣
8. ብር 4,555,260.87 ለመምህራን የሥራ ጫና (ኦቨርሎድ) እና የትርፍ ሰዓት ክፍያ ለተፈጸመው የቀረበው ማስረጃ ትምህርት ሚ/ር ለሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች የፃፈውን መሠረት በማድረግና ለኢንስቲትዩቱ የተፃፈ ማስረጃ ሳይኖር ተከፍሎ መገኘቱ፣
9. በድምር ብር 1,750,077.44 ከውጭ መምህራን ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ላይ የሥራ ግብር ሳይቀነስ (ሳይሰበሰብ) ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፣
10. ብር 3,182,405.12 ገንዘቡ ወጪ ለመሆኑ የወጪ ሰነዶች ለኦዲት ባለመቅረባቸው የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣
11. በድምሩ ብር 78,256,261.03 ተሰብሳቢ ሂሳብ በወቅቱ ሳይወራረድ የተገኘ መሆኑ፣
12. በድምሩ ብር 1,569,345.80 ተከፋይ ሂሳብ ለሚመለከተው አካል ሳይከፈል መገኘቱ፣
13. ብር184,334,927.00 ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ መሆኑ ፣

ከላይ ከተራ ቁጥር ከ1 እስከ 14 በተገለጹት ጉልህና በሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መግለጫዎች ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም. የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳይም፡፡

ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፣

ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊደረግባቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል::

- መኪና ሰርቪስ የተደረገበት አገልግሎት ለሞኤንኮ የተከፈለ ብር 17,717.77 አገልግሎቱ በባለሙያ ሳይረጋገጥ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፣
- ኢንስቲትዩቱ ለሚሰበስበው ገቢ የገቢ እቅድ ያላዘጋጀ መሆኑ፣

- ብር 5,519,082.08 በወጪ ማስመስከሪያ ደረሰኞች ላይ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት በጀት ስለመኖሩ በፊርማ ያልተረጋገጠ መሆኑ፣

- ብር 4,651,000.00 ወጪ በውስጥ ገቢ የፋይናንስ ምንጭ 1900 በጀቱ በተፈቀደው መሰረት መያዝ ሲገባው ከመንግስት ግምጃ ቤት የፋይናንስ ምንጭ 1800 ከተፈቀደው ጋር ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፣

በጀት፣

- ብር 150,576,883.00 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት መኖሩ፣

ሌሎች ጉዳዮች፣

- **ንብረት፣**
  - የአላቂ ዕቃ እና የቋሚ ዕቃ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞዴል/19 እና የንብረት ወጪ ደረሰኝ ሞዴል/22 የሚዘጋጀውና የሚመዘገበው በአላቂ ዕቃ ግምጃ ቤት ሠራተኛ መሆኑ፣
  - በተጠቃሚዎች እጅ ላይ የሚገኙ ቋሚ ንብረቶች መቆጣጠሪያ ካርድ (User Card) በሁለት ቅጅ ተዘጋጅቶ አንዱ ለተጠቃሚው ሌላው በንብረት ክፍል የሚያዝ ነው፡፡ ሆኖም የመ/ቤቱ ንብረት ክፍል የሚሰራበት አለመሆኑ፣
  - የተቆጠሩት ቋሚ ዕቃዎች ከስቶክ ካርድና ከተጠቃሚዎች እጅ ላይ የሚገኙ ቋሚ ንብረቶች መቆጣጠሪያ ካርድ (User Card) ከተመለከተው ጋር የማስታረቅና የማመሳከር ሥራ ለመሰራቱ ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣
  - ቋሚ ዕቃዎች በተሟላ ሁኔታ መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፣
  - የተለያዩ የመኪና ጎማዎች በቁጥር 20፣ ኮምፒዩተር ብዛት 7፣ ፕሪንተሮች ብዛት 4፣ ፎቶ ኮፒ ማሽኖች ብዛት 2፣ ፋክስ ማሽን ብዛት 1 እና የተለያዩ ቁርጥራጭ ብረታብረቶች አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች መኖራቸው፣

ልዩ ልዩ፣

- ኢንስቲትዩቱ ለሥራ አገልግሎት የሚውል የቀጥታ ስልክ መስመር ለቁጥጥር እንዲያመች በየሥራ ክፍሉ የሚጠቀሙበት የስልክ ሂሳብ ተመን ያልተሰጠ መሆኑ፣

- ኢንስቲትዩቱ ከተፈቀደለት 361 የስራ መደቦች ውስጥ በሰው ኃይል የተሞላው 157 ሲሆን 204 (56%) የሥራ መደቦች ክፍት መሆናቸው፣
- ኢንስቲትዩቱ የስጋት ምንጮች መለየት እና የስጋት ተጋላጭነት ፍተሻ ያላደረገ መሆኑ፣
- በ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ላይ ለተሰጠው የኦዲት አስተያየት እርምጃ ሳይወሰድ የተገኘ በተለያዩ የባንክ ወጪ ማስመስከሪያዎች እና የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣዎች በድምሩ ብር 3,168,870.89 የተከፈለው የወጪ ሰነዶች ያልቀረቡለት ሂሳብ መሆኑ፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት
የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች

መግቢያ፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ ኢንስቲትዩቱን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓለማ፣

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የኢንስቲትዩቱ የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሰረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመስራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን ፣

- የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ ሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ፣ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

ቀጥለው በተመለከቱት የኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለመስጠት በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡

ይሁን እንጂ ኦዲቱ የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኢንስቲትዩቱ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. **የገቢ ሂሣብ፣**

1.1.1 **ግኝት፣ ከተከታታይ ትምህርት ለሚሰበሰበው ገቢ የገቢ ዕቅድ አለመቅረቡ፤**

በፌዴራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6 መሰረት ኢንስቲትዩቱ ለሚሰበስበው ገቢ የገቢ ዕቅድ ማዘጋጀቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ኢንስቲትዩቱ ለሚሰበስበው ገቢ የገቢ እቅድ ያላዘጋጀ መሆኑ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

1.1.2 **ስጋት፣**

- የቁጥጥርና የክትትል ሥርዓቱ የተዳከመ ሊሆን ይችላል፡፡
- የተሰበሰበው ገቢ በዕቅዱ መሰረት መሆኑን ለመከታተል አያስችልም፡፡

1.1.3 **የማሻሻያ ሀሳብ፣**

ኢንስቲትዩቱ ለወደፊቱ ለሚሰበሰበው ገቢ የገቢ ዕቅድ ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

1.1.4 **የስራ አመራሩ ምላሽ፣**

የስራ አመራሩ የማሻሻያ ሀሳቡን ተቀብሎታል፡፡

1.2.1 **ግኝት፣ በመመሪያው መሰረት ያለቅጣት የተከፈለ ክፍያ፣**

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 16.26 ውል መፈረም ንዑስ አንቀጽ 16.27.4 በንዑስ አንቀጽ 16.27.3 መሰረት (ሸ)አቅራቢው በውሉ በተመለተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን ባያስረክብ (ሀ) አቅራቢው ሳይፈፅም በቀረው የውል መጠን ላይ በየቀኑ 1/100 ወይም 1/1000 የጉዳት ካሳ መክፈል እንዳለበት ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ

1. ለኢንሰትትዩቱ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0795980 የማሰተማሪያ እቃዎች ግዥ ከኤም ኤም አሰመጪ ዕቃው ተገዝቶ ክፍያ ተፈፅሟል ሆኖም ድርጅቱ ውል ከተፈረመበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር 90 ቀናት ውሰጥ ዕቃውን ለማቅረብ ቢሰማማም አቅራቢው ዕቃውን የሚያቀርብበት የመጨረሻ ቀን ነሐሴ 24/2008 ሆኖ ውል የተፈረመው 25/09/2008 ዕቃው በሞዴል 19 ገቢ የሆነው ያለቅጣት 07/02/2009 በመሆኑ፡፡ ውል ከገባበት ጊዜ ጀምሮ በላይ ላዘገየበት ብር 239,556.50*1/1000*41 = ብር **9,821.81** የጉዳት ካሣ ያልተቀነሰ በመሆኑ፡፡

2. ለነብዩ ማሞ ህንፃ ተቋራጭ ለላንድ ሰኬፑ አገልግሎት (ግቢ ማስዋብ) ለተከፈለው ሂሳብ ብር 12,178,886.01 ሲሆን ውሉ የተገባው 27/10/08 በውሉ መሰረት 180 ቀን (6 ወር) ሲሆን በዚህ መሰረት ውሉ የሚጠናቀቀው 27/04/09 ድረስ ስራውን አጠናቆ ማስረከብ ሲኖርበት እስከ 29/10/2009 ስራው ያልተጠናቀቀ ሲሆን ኢንስቲትዩቱ ላጋጠመው መጓተት ተቋራጭ ላዘገየበት ስድስት ወር (180 ቀናት ቅጣት 180*0.001*12,178,886.01=ብር 2,192,199.40) የቅጣት ገንዘብ ነው ፡፡ ሆኖም የቅጣት ገንዘብ የውሉን 10% መብለጥ ስለሌለበት ብር 12,178,886.01*10= ብር **1,217,888.60** የቅጣት ገንዘብ ሳይሰበሰብ ቀርቷል፡፡

በድምሩ ብር **1,227,710.41** የጉዳት ካሳ ያልተቀነሰ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

1.2.2 ስጋት፣

- በመመሪያው መሠረት ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘት፣ ይህም ቁጠባን፣ የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማረጋገጥ አይቻልም፣ የመንግሥትም ገንዘብ ለብክነትና ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላል፡፡ እና
- ለመንግሥት ገቢ መሆን የነበረበት ገቢ እንዳይገባ ከማድረጉም ባሻገር አፈፃፀሙ ለብልሹ አሰራር በር እንዲከፍት እና እንዲጋለጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

1.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- ኢንስትትዩቱ በመመሪያው መሠረት ለመፈጸሙ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ የሚጠበቅበት ሲሆን ከላይ ከመመሪያው ውጭ ለተፈጸመው ክፍያ አስፈላጊው አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡
- ያልተሰበሰበው ቅጣት ብር 1,227,710.41 ገቢ እንዲሆን ተደርጎ ለወደፊቱ ኃላፊነታቸውን በማይወጡት ላይ በመመሪያው መሠረት በአግባቡ ሊቀጣቸው የሚገባ ሲሆን በተደጋጋሚ ኃላፊነታቸውን የማይወጡትን ደግሞ ለመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በማሳወቅ ተጨማሪ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

1.2.4 የስራአመራሩ ምላሽ፣

- በወቅቱ ምላሽ ሰጥተንበታል፤ ለዚሁም ምላሽ የተሰጠበትን አያይዘናል ለተባለው የተያያዘው ምላሽ የዘገየበት ጊዜ 41 ቀናት በመሆኑ ግዥ ኤጀንሲ የ41 ቀናት ቅጣት ብር 9, 821.81 በጽሁፍ ማረጋገጫ እንደሚሰጡ ተግባብተናል ብለዋል፡፡

- አማካሪ ድርጅቱ በሚሰጠው ማረጋገጫ መሠረት ወደፊት በማያዣነት ከተቀመጠው ሂሣብ ላይ ተቀናሽ እናደርጋለን ብለዋል፡፡

1.3.1 <u>ግኝት፣</u> <u>በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ ገቢ፣</u>

ኢንስቲትዮቱ የሚሰበሰው የገቢ ሂሳብ በትክክለኛ የገቢ የሂሳብ መደብ መሰረት የተመዘገበ መሆኑን ለማረጋገጥ አዲት ሲደረግ፡-

ብር 8,214,759.93 ከትምህርት ክፍያ፣ የጨረታ ማስያዣ፣ ለፈተና መፈተኛ፣ ለቅጣትና ከሌሎች የተሰበሰበ ገቢ ኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መደብ (Chart Of Account) መሰረት የሙያና የትምህርት ተቋም የሚሰበሰብ ገቢ 1443 እና ከልዩ ልዩ የተሰበሰበ ገቢ ደግሞ 1489 ተለይተው መመዝገብ ሲገባው፣ ገቢው በሂሳብ መደብ 1489 በጥቅል ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

1.3.2 <u>ስጋት፣</u>

ኢንስቲትዮቱ የፋይናንስ ደንብን ተከተሎ በትክክለኛ የሂሳብ መደብ ካልመዘገበ የሚቀርበውን የሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛነቱን አጠራጣሪ ሊያደርገው ይችላል፡፡

1.3.3 <u>**የማሻሻያ ሀሳብ፣**</u>

ኢንስቲትዮቱ ሂሳቡ የፋይናንስ ደንብን ተከተሎ በተፈቀደው የሂሳብ መደብ (Chart of Account) መሰረት በትክክለኛ የሂሳብ መደብ እንዲመዘገብ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

1.3.4 <u>የስራአመራሩ ምላሽ፣</u>

በ2010 የምዝገባ ማስተካከያ ያደረግን በመሆኑ የተማሪዎች የማታ፣ የቅዳሜና የእሁድ እንዲሁም የክረምት ከመማር ማስተማሩ የሚሰበሰበው በገቢ ሂሳብ ኮድ 1443 እንዲመዘገብ ተደርጓል ብለዋል፡፡

2. <u>**የወጪ ሂሣብ ፣**</u>

2.1.1 <u>ግኝት፣</u> <u>ያለበጀት ዓመቱ የተመዘገበ ሂሳብ፣</u>

የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 140 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የመደበኛ እና የካፒታል የስራ ማስኬጃ ወጪዎች ሲፈጸም ወጪው ለሚደረግበት ተግባር በበጀት ዓመቱ የተያዘ ወይም ወጪውን ለመሸፈን ቀሪ በጀት መኖሩንና ወጪው በመስሪያ ቤቱ ዕቅድ ውስጥ የተያዘና በጥሬ ገንዘብ ፍላጎት ላይ የተካተተ መሆኑ ሳይረጋገጥ ወጪ መፈፀም እንደማይገባ መመሪያዉ ይገልፃል፡፡ በዚህም መሰረት የወጪ ሂሳቦች የሚመዘገቡት በ2009 በጀት ዓመት በተፈቀደው የበጀት ድልድል መሰረት

መሆኑንና የበጀት ዓመቱ ሂሳብ በበጀት ዓመቱ የሚመዘገብ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ስካይ ሩሊንግ የተለያዩ ፈርኒቸሮች ተገዝተው በንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞ/19 ንብረቱ ገቢ የሆነው በ28/10/08 ሲሆን ወጪው በ22/11/2008 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0795443 በሂሳብ መደብ 6313 ብር 1,733,855.00 ከበጀት ዓመቱ ውጭ ተመዝግቦ የተገኘ፣ ከኢትዮ ቴሌኮም የቀረበው ማስረጃ የጥቅምት 2008 የስልክ ክፍያ ሲሆን ወጪው በ15/09/09 የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 203274 በሂሳብ መደብ 6258 ብር 176,914.25 በ2009 በጀት ዓመት ተመዝግቦ የተገኘ ፣ በ2008 በጀት ዓመት በሂሳብ መደብ 6256 የተያዘ የአገልግሎት ግዥ የተከፈለ ሲሆን ወጪው በቀን 30/04/09 የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 58795 ብር 3,403.08 ተመዝግቦ የተገኘ፣ ከመጋቢት እስከ ግንቦት 2008 የውሃ አገልግሎት የተከፈለ ሲሆን ወጪው በቀን 02/13/08 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0795571 ብር 655,473.76 ተመዝግቦ የተገኘ፣ ከኢትዮ ቴሌኮም የቀረበው ማስረጃ የ2008 የስልክ ክፍያ ሲሆን ወጪው በቀን 03/01/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0795589 ብር 750,621.36 የተከፈለ ተመዝግቦ የተገኘ ሲሆን በድምሩ ብር **3,320,267.45** በ2008 በጀት ዓመት መያዝ ሲገባው በ2009 በጀት ዓመት የተመዘገበ መሆኑ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

2.1.2 ስጋት፣

የበጀት ዓመቱ የሂሳብ መግለጫ ትክክለኛውን የበጀት ዓመቱን ወጪዎች እንዳያመለክት ምክንያት ሊሆን ከመቻሉም በተጨማሪ በ2009 በጀት ዓመት ዕቅድ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

2.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የበጀት ዓመቱ ሂሳብ በበጀት ዓመቱ እንዲወራረድ ተገቢ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.1.4 የስራአመራሩ ምላሽ፣

- የ2008 በጀት ዓመት በመጠናቀቁ ለመምህራን መኖሪያ ቤት ግንባታ ለኮንትራክተሮች ቅድመ ክፍያ ለመክፈል ሲባል በዚህ በጀት ስላልነበረ ወደሚቀጠለው በጀት ዓመት ሊተላለፍ ችሏል፡፡

- መክፈል የነበረበት ከበጀት ዓመቱ የዞረ ሂሳብ በመሆኑ ክፍለናል የግዴታ ሂሳብ በመሆኑ የበጀት ዓመት ሳያልፍ ክፍያ እንዲጠይቁን ብናደርግም ኢትዮ ቴሌኮም በወቅቱ ባለመጠየቁ ክፍያ እንድንፈጽም ተገደናል፡፡ በማት ገልፀዋል፡፡

2.1.5 <u>የኦዲተሩ አስያየት፤</u>

በስራ አመራር ምላሹ ላይ የ2008 በጀት ዓመት በመጠናቀቁ ለመምህራን መኖሪያ ቤት ግንባታ ለኮንትራክተሮች ቅድመ ክፍያ ለመክፈል ሲባል በዚህ በጀት ስላልነበረ ወደሚቀጥለው በጀት ዓመት የዞረ ነው ለተባለው ቅድመ ክፍያ ሳይሆን ፊርኒቸሮች ተገዝተው በንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞ/19 ንብረቱ ገቢ የሆነው በ28/10/08 ሲሆን ወጪው በ22/11/2008 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0795443 በሂሳብ መደብ 6313 ብር 1,733,855.00 ከበጀት ዓመቱ ውጭ ተመዝግቦ የተገኘ ነው፡፡ ስለሆነም ለወደፊት የበጀት ዓመቱ ሂሳብ በበጀት ዓመቱ እንዲወራረድ ተገቢ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

2.2.1 <u>ግኝት፤</u> <u>በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘበ ሂሳብ፤</u>

የገቢና የወጪ ሂሳቦች የሚያዙትና የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ግንቦት 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት በተገቢው የሒሳብ መደብ የሚመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ብር 20,426,911.53 በተገቢው የሂሳብ መደብ ሳይመዘገቡ ተገኝተዋል፡፡

2.2.2 <u>ስጋት፤</u>

ትክክለኛውን የወጪ ሂሳብ እንዳያሳይ ሊያደርግ ከመቻሉም በተጨማሪም የሂሳብ መግለጫውን ተዓማኒነት ሊያሳጣው እና የበጀት አጠቃቀም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊሳድር ይችላል፡፡

2.2.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

ወጪዎች ከመመዝገባቸው በፊት ለወጪው በጀት መያዙንና የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ያወጣውን የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ተከትሎ በተገቢው የሂሳብ መደብ መያዛቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡

2.2.4 <u>የስራአመራሩ ምላሽ፤</u>

- ለወደፊቱ መመዝገብ ባለበት የሂሳብ መደብ ተገቢውን ማስተካከያ እንሰራለን፤

- በሂሳብ ኮድ 6251 የተመዘገበው በ6324 መመዝገብ ቢኖርበትም በዚህ ኮድ የተፈቀደ በጀት ባለመኖሩና በወቅቱም በበጀት ዝውውር ተገቢው ማስተካከያ ማድረግ ቢቻልም በሥራ ብዛት ባለመደረጉ ይህ ለወደፊቱ የሚስተካከል ነው ብለዋል፡፡

2.3.1 ግኝት፣ አገልግሎት ለማግኘቱ በራሱ ባለሙያ የተረጋገጠበት ማስረጃ ያልቀረበ፣

የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 9 ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች በቁጥር 2/ ዕቃው ወይም አገልግሎቱ በተፈላጊ ባህርያት ዝርዝር (specification) መሰረት መቅረቡን ወይም አገልግሎት መስጠቱን፣ በቁጥር 4/ አስፈላጊ ሲሆን ዕቃው ወይም አገልግሎቱ በትክክል ለመቅረቡ ወይም ለመሰጠቱ ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች የፅሁፍ ማረጋገጫ መቅረብ እንዳለበት መመሪያው ያዛል፡፡ በዚህም መሰረት በበጀት ዓመቱ የተጠገኑ ተሽከርካሪዎች በትክክል ተጠግነው በመስሪያ ቤቱ ባለሙያ ተረጋግጦ ገቢ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የአገልግሎት ግዥዎች በቀን 26/04/2009 የወጪ ቫውቸር ቁጥር 0796507 የሂሳብ 6241 የሰሌዳ ቁጥር 4-22407 የተሰጠው አገልግሎት ለመኪና ሰርቪስ የተደረገበት ለአገልግሎት ለሞኤንኮ የተከፈለ ብር 17,717.77 አገልግሎቱ በባለሙያ ሳይረጋገጥ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑን በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

2.3.2 ስጋት፣

የአገልግሎትም ሆነ የዕቃ ግዥ በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት በትክክል ለመሰራቱ በባለሙያ ሳይረጋገጥ ክፍያ መፈፀም አላግባብ ወጪ ሊያስወጣ ይችላል፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን በባለሙያዎች ሳይረጋገጥ ንብረቱ ገቢ ከሆነ ዕቃዎቹ መገልገል የሚገባቸውን ጊዜ ሳያገለግሉ ለብልሽት ሊዳረጉ ይችላሉ፡ :

2.3.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ኢንስትትዩቱ ማናቸውም የዕቃና የአገልግሎት ዕቃው ወይም አገልግሎቱ በትክክል ለመቅረቡ ወይም ለመሰጠቱ በሚመለከታቸው ባለሙያዎች የፅሁፍ ማረጋገጫ መቅረቡን መረጋገጥ ይኖርበታል ::

2.3.4 የስራአመራሩ ምላሽ፣

ሞኤንኮ ለሰርቪስ የሚገቡ መኪናዎች የጥገና አገልግሎት ሳይሆን የሰርቪስ አገልግሎት ብቻ የሚሰጡ በመሆኑ ወደ ንብረት የሚገባ ዕቃ የሌለ ሲሆን መኪናዎች በትክክል ሰርቪስ ለመደረጋቸው ሞኤንኮ ያስገባው አካል አረጋግጦ ፈርሞ የሚያስረክብ ቢሆንም

ያረጋገጠበት ሰነድ ሰርቪሱን ከሰጠው ተቋም /ሞኤንኮ/ ላይ የሚቀመጥ መሆኑን እየገለጽን ለቀጣይ ግን ከክፍያ ሰነድ ጋር አብሮ እንዲያያዝ እናደርጋለን ብለዋል፡፡

2.4.1 **ግኝት፣በውል ስምምነት ከተገለፀው በላይ የተከፈለ የግንባታ ሂሳብ፣**

ክፍያዎች የሚፈጸሙት አገልግሎቱ የደረሰበትን ወይም የተከናወነውን የአገልግሎት ደረጃ //በውሉ መሠረት ለተጠናቀቀው አገልግሎት/ የሚገልጽ የክፍያ ምስክር ወረቀት ሲቀርብ ብቻ ለመሆኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከነብዩ ማሞ ህንፃ ተቋራጭ ለላንድ ስኬፕ (ለግቢ ማስዋቢያ) አገልግሎት በውሉ መሰረት መከፈል ያለበት ክፍት ጋር ብር 12,178,886.01 ሲሆን በተለያየ ወጪ ማስረጃ ተከፍሎ የተገኘ ብር 14,418,471.37 ሲሆን የውሉ ጊዜ የተጠናቀቀው ቀን 27/04/09 ሲሆን ተጨማሪ ውል የተገባበት ሰነድ ሳይቀርብ እስከ 29/10/09 ክፍያ እየተፈፀመ ቆይቶ ከውል በላይ ብር 2,239,585.36 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

2.4.2 **ስጋት፣**

ተቋራጩ በተከፈለው ክፍያ መጠን የተገባ ውል ወይም የተሰጠ የተጨማሪ ስራ ትዕዛዝ ሳይኖር ክፍያ መፈጸም የመንግሥት ገንዘብ አላግባብ ወጪ እንዲሆን መንገድ ሊከፍት ይችላል፡፡

2.4 3 **የማሻሻያ ሀሳብ፣**

ኢንስቲትዩቱ ተጨማሪ ውል ገብቶ ክፍያው የተፈፀመ ከሆነ የተጨማሪ ውል ስምምነት የተደረገበት ሰነድ እንዲቀርብ ካልሆነ አለአግባብ የተከፈለው የተቋራጩ ሂሳብ ተመላሽ እንዲደርግና ሌላም ተመሳሳይ ሁኔታ አለመኖሩን ተጣርቶ በሚገኘው ውጤት መሠረት እርምጃ እንዲወሰድ፣ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ጉዳዩ የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ጥብቅ ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

2.4.4 **የስራአመራሩ ምላሽ፣**

የስራ አመራሩ የማሻሻያ ሀሳቡን ተቀብሎታል፡፡

2.5.1 **ግኝት፣ የተሰረዘ የወጪ ቫውቸር በሂሳብ እንቅስቃሴ ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ፣**

የፌዴራል መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 1'ሀ' መሠረት የመንግስት መስሪያ ቤቶች ከበጀት ሥርዓት ጋር አብሮ የሚሄድ በጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ ላይ የተመሠረተ የተሻሻለ የጥንድ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መጠቀም ይኖርባቸዋል ይላል፡፡ ሆኖም ኢንስቲትዩቱ በቀን 30/10/2009 በItem No 6872 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር

534010 ብር 10,573.00 የተሰረዘውን የወጪ ቫውቸር በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (TR) የተመዘገበ መሆኑ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

2.5.2 ስጋት፣

የተሰረዙት ወጪዎች በሂሳብ እንቅስቃሴ መዘገብ ላይ መመዝገባቸው በሂሳብ መደብ 6253 የተያዘው ወጪ ከፍ ብሎ ሊታይ ይችላል::

2.5.3 የማሻሻያ ሃሳብ፣

ወጪዎች ከመመዝገባቸው በፊት የተሰረዙት የወጪ ማስመስከሪያዎች በትክክል የተሰረዙ መሆናቸውን በማረጋገጥ በጊዜው ማስተካከያ እንዲሰራላቸው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.5.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

የተሰረዘ ቫውቸር ተመዝግቦ ሲገኝ ማስተካከያ ሊሰራለት የሚገባው መሆኑን ተረድተናል፡፡ ሆኖም ስህተቱን ተቀብለን ለወደፊቱ ጥንቃቄ በማድረግ እናስተካክላለን ብለዋል፡፡

2.6.1 ግኝት፣ ዝርዝር የወጪ ማሰረጃ ሳይቀርብለት በወጪ የተመዘገበ፣

በፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀፅ14 ንዑስ አንቀፅ 4 መሠረት ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጪዎች ተገቢው የሠነድ ማስረጃ መቅረብ ያለበት መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ሆኖም ኢንስቲትዩቱ የሚጠቀምባቸው የመደበኛ ስልክና የኢንተርኔት ክፍያ ዝርዝር ክፍያው ሳይቀርብ በጥቅል ብር 919,897.99 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

ክፍያው ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ተራ ቁጥር	ቀን	የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር	የ[illegible]ጪ ምክንያት	ወጪው የተመ[illegible]ገ[illegible]በት[illegible]ሂሣብ መደብ	የ[illegible]ንዘቡ ልክ	
1.	02/10/09	0796064	የመጋቢትና ሚያዝያ/09 የኢንተርኔትና የስልክ ክፍያ	625[illegible]	297,816	66
2	13/07/[illegible]9	0798087	የየካቲት/09 የኢንተርኔትና የስልክ ክፍያ	‹‹	148,249	76
3	01/07/0[illegible]	[illegible]798031	የጥር/09 የኢንተርኔትና የስልክ [illegible]ክፍያ	‹‹	147,933	46
4	29[illegible]10[illegible]09	[illegible]7956[illegible]7	የግንቦት/09 የኢንተርኔትና የስልክ ክፍያ	‹‹	148,983	86

5	15/09/09	203274	የጥቅምት/2008 የተከፈለ የስልክ ክፍያ የተከፈለ	‹‹	176,914	25
			ጠ[illegible]ላላ ድምር		**919,897**	**99**

2.6.2 ስጋት፣

- የወጪውን ሂሣብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ካለማስቻሉም በተጨማሪ የመንግሥት ገንዘብ አላግባብ ወጪ ሊሆን ይችላል።
- የኢንስቲትዩቱ የስልክ አገልግሎት ላልተጠቀመበት ሂሳብ ክፍያ ሊከፈል ይችላል።
- የስልክ ሂሳበ አላግባብ ከፍ ብሎ ሊታይ ይችላል።

2.6.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ለክፍያው በዝርዝር እያንዳንዱ ስልክና ኢንተርኔት በወር የቆጠረውና የገንዘብ ልክ የሚያሳይ የሂሳብ ክፍያ ማስረጃ ሊቀርብለት ይገባል። በተጨማሪም ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት የተሟላ ማስረጃ መቅረቡ በማረጋገጥ ክፍያ እንዲፈጸም ተገቢ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል።

2.6.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

የኢንስቲትዩቱ የቀጥታ መስመር ስልኮች የክፍያ ጥያቄ ሲቀርብ የትኛው የስልክ ቁጥር ምን ያህል በወር እንደቆጠረ ለማወቅ ከኢትዮ ቴሌኮም መሥሪያ ቤት በመነጋገርና ማስረጃ ለማግኘት በጥረት ላይ ብንገኝም ሙሉ መረጃ ለማግኘት ጊዜ ወስዷል፡፡ ለወደፊቱም የቀጥታ ስልክ አጠቃቀም ኖርም በማውጣት ላይ ስለምንገኝና ይህንንም ለወደፊቱ የምናደርግ መሆኑን እንገልጻለን ብለዋል፡፡

2·7·1 ግኝት፣ለመምህራን ለኦቨር ሎድ እና የትርፍ ሰዓት ክፍያ፣

ኢንስቲትዩት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 245/2003 ራሱን የቻለ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ የተቋቋመ መሆኑ በደንቡ ላይ የተገለጸ ቢሆንም ኢንስቲቲዩቱ ብር 4,555,260.87 ለመምህራን ኦቨር ሎድ እና የትርፍ ሰዓት ክፍያ ለፈጸመው የቀረበው ማስረጃ የመምህራን ኦቨር ሎድ እና ትርፍ ሰዓት ክፍያ ትምህርት ሚ/ር ለሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች የፃፈውን እንጂ ለኢንስቲትዩቱ የተፃፈ አልቀረበም።

2.7.2 ስጋት፣

ማንኛውም ክፍያ በመንግስትን ደንብና መመሪያ መሰረት ተግባራዊ ካልሆነ የመንግስት ሀብት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል።

2.7.3 የማሻሻያ ሃሳብ፤

ኢንስቲትዩት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 245/2003 ራሱን የቻለ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ የተቋቋመ መሆኑ በደንቡ ላይ የተገለጸ ቢሆንም የቀረበው የመምህራን ትርፍ ሰዓት ክፍያ ትምህርት ሚ/ር ለሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች የፃፈው እንጂ ለኢንስቲትዩቱ የተፃፈ ያልቀረበ በመሆኑ ሊቀርብ ይገባል፡፡

2.7.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

የትምህርት ሚኒስቴር እንዲከፈል የተፈቀደበትን መመሪያ ቅጅ ሁለት አባሪ በማድረግ አያይዘናል፣ በተጨማሪም፣

በደንብ ቁጠር 245/2003 የከፍተኛ ትምህርት አካል ሆኖ የተቋቋመ በመሆኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማግኘት ያለባቸውን ጥቅማ ጥቅም በተሰጠው ደንብ ቁጥር መሠረት ያገኛል ለማስረጃ ይሆን ዘንድ 5 ገጽ ቅጂ አባሪ አያይዘናል ብለዋል፡፡

2.7.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

በስራ አመራር ምላሹ ላይ እንደተጠቀሰው የትምህርት ሚኒስቴር ለሌሎች ዩኒቨርስቲዎች እንዲከፈል የተፃፈው ደብዳቤ ታይቷል ሆኖም ለኢንስቲትዩቱ በስሙ የተፃፈለት ያልቀረበ በመሆኑ ሊቀርብ ይገባል፡፡

2.8.1 ግኝት፣ ከውጭ መምህራን ከቅጥር ከሚገኝ ገቢ ያልተቀነሰ ስራ ግብር፣

በገቢ ግብር አዋጅ 979/2008 ዓ/ም ክፍል ሁለት አንቀጽ 9 ማንኛውም ገቢ የሚያገኝ ሰው በዚህ አዋጅና በታክስ አስተዳደር አዋጅ መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት ይላል፡፡ ይሁን እንጂ ኢንስቲትዩቱ በኮንትራት ውል በመቅጠር የሚያሰራቸውን የውጭ ሀገር ዜጎች በዓለም አቀፍ ስምምነት መሠረት ከግብር ነፃ መሆናቸውን የሚገልጽ ማስረጃ ሳይኖር በድምሩ ብር1,750,077.44 ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ላይ የሥራ ግብር ሳይቀነስ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

2.8.2 ስጋት፣

- መንግስት ማግኘት የሚገባውን ግብር እንዳያገኝ ሊያደርግ ይችላል፡፡
- መንግስት ያወጣውን የግብር አዋጅ ተከትሎ ያለመሥራት ተጠያቂነትን ሊያመጣ ይችላል፡፡

2.8.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ኢንስቲትዩቱ በኮንትራት ውል በመቅጠር የሚያሰራቸውን የውጭ ሀገር ዜጎች በዓለም አቀፍ ስምምነት መሠረት ከግብር ነፃ መሆናቸውን የሚገልጽ ማስረጃ ሊቀርብ ካልቻለ ተቀናሽ ያልተደረገው የሥራ ግብር ከሚመለከታቸው ሠራተኞች ተመላሽ ተደርጎ ለግብር አስገቢው መሥሪያ ቤት ገቢ መደረግ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም በወጣው አዋጅና ደንብ መሠረት ተቀናሽ እንዲደረግ ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

2.8.4 የስራአመራሩ ምላሽ፣

በኢንስቲትዩቱ የተቀጠሩ መምህራን ከሥራ ግብር ነጻ እንደሚከፈሉና በውሉ የተካተተ በመሆኑ ክፍያውም እየተፈጸመ ያለው በውላቸው መሠረት መሆኑን እንገልጻለን ብለዋል፡፡

2.8.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

በስራ አመራር ምላሹ ላይ እንደተገለፀው ውሉ ከሥራ ግብር ነፃ የሚል መሆኑ ታይቷል፡፡ ሆኖም ሀገርን ተጠቃሚ ለማድረግ ቅጥር በሚፈፀምበት ወቅት የሥራግብር መክፈል ያለባቸው መሆኑ ተገልፆላቸው ውሉ ቢዘጋጅና ክፍያ ቢፈፀም ካልሆነም በዓለም አቀፍ ስምምነት መሠረት ከግብር ነፃ መሆናቸውን የሚገልጽ ማስረጃ ሊቀርብ ይገባል፡፡

2.9.1 ግኝት፣ለኦዲት ያልቀረቡ የወጪ ሰነዶች፤

የፌደራል መንግስት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ6 የመንግስት መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ የፋናንስ ኃላፊነቶች የሂሰብ አያያዝ በሚመለከት የመስሪያ ቤቱ የፋይናስ ሠነዶችና መዛግብት አቅርቦ ኦዲት የማስደረግ ኃላፊነት እንዳለበት ይገልጻል ይሁን እንጂ በኢንስቲትዩቱ ወጪ ለሆነው ብር 3,182,405.12 ገንዘቡ ወጪ ለመሆኑ የወጪ ሰነዶች ለኦዲት ባለመቅረባቸው የወጪውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

2.9.2 ስጋት፣

- የወጪ ማስረጃዎች ባለመቅረባቸዉ የክፍያዉን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አይቻልም፡፡
- የመንግስት ገንዘብ ለታቀደለት ዓላማ ላይውል ይችላል፡፡

2.9.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የወጪ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ እንዲቻል ተገቢዉ የሂሳብ ሰነድ ትክክለኛውን የሰነድ አቀማመጥ ዘዴ ተከትሎ በአግባቡ ሊቀመጥና በተፈለገ ጊዜ በወቅቱ ለማቅረብ እንዲቻል ሊያመቻች ይገባል፡፡

2.9.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የወጪ ሰነዶች የሚለው የወጪ ሰነድ ሳይሆን የማስተካከያ ሂሣብ የተሰራበት ስለሆነ ለዚሁም ማስረጃዎቹን አያይዘን ልከናል ብለዋል፡፡

2.9.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

በስራ አመራር ምላሹ ላይ እንደተገለው ለኦዲት ያልቀረበው የወጪ ሰነዶች የሚለው የወጪ ሰነድ ሳይሆን የማስተካከያ ሂሣብ መሆኑንና ማስረጃዎቹን አያይዘን ልከናል የሚል ነው፡፡ ሆኖም ተያያዘ የተባለው ማስረጃ ፕሪንት የተደረገ የሂሳብ መመዝገቢያ መዝገብ (TR) እና የሂሳብ ቋት (Ledger) እንጂ የሂሳብ ሰነዶቹ ማለት የወጪ ማስመስከሪያ ሰነድ (PV) ወይም የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ሰነድ (JV) ስላልሆነ ለወደፊት የሂሳብ ሰነዱ ለኦዲት ሊቀርብ ይገባል፡፡

2.10.1 <u>ግኝት፣</u> <u>በወጪ ማስመስከሪያ በጀት ስለመኖሩ ሳይረጋገጥ የተከፈለ፣</u>

የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 3/2003 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 6 ማንኛቸውም የሳጥንና የባንክ ሂሳብ ወጪ ከመሆኑ በፊት በጀት ስለመኖሩ በቅድሚያ የሚረጋገጥ መሆኑን በፋይናንስ መመሪያው ላይ በተመለከተው መሰረት ሁኔታውን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ ብር 5,519,082.08 በወጪ ማስመስከሪያ ደረሰኞች ላይ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት በጀት ስለመኖሩ በፊርማ ያልተረጋገጠ መሆኑ ታውቋል፡፡

2.10.2 <u>ስጋት፣</u>

ለየሂሳብ መደቦቹ (ኮዶች) የተፈቀደ በጀት ሳይኖር ክፍያ ሊፈጸም ይችላል፡፡

2.10.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ለወጪው በጀት የተያዘ ለመሆኑ በቅድሚያ በወጪ ማስመስከሪያ ደረሰኞቹ ላይ እንዲረጋገጥ መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.10.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

በወቅቱ የሰው ኃይል ክፍተት ስለነበረው ፊርማ ያልተፈረመ ሲሆን ለቀጣዩ ጊዜ ግን ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት በጀት መኖሩ በፊርማ እየተረጋገጠ መሄድ እንዳለበት የተሰጠውን አስተያየት በመቀበል የምናስተካክል መሆኑን እንገልጻለን ብለዋል፡፡

2.11.1 **ግኝት፣ ወጪው በውስጥ ገቢ የፋይናንስ ምንጭ መያዝ ሲገባው በመደበኛ የተያዘ ሂሳብ፣**

ብር 4,651,000.00 ወጪ በውስጥ ገቢ የፋይናንስ ምንጭ 1900 በጀቱ በተፈቀደው መሰረት መያዝ ሲገባው ከመንግስት ግምጃ ቤት የፋይናንስ ምንጭ 1800 ከተፈቀደው ጋር ሪፖርት የተደረገ መሆኑን በኦዲት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

2.11.2 **ስጋት፣**

በበጀት ዓመት መጨረሻ በባንክ ያለው የውስጥ ገቢ ሲተላለፍ በትክክል በፋይናንስ ምንጭ በውስጥ ገቢ 1900 ተለይቶ ካልተመዘገበ ገንዘቡ ላልታለመለት ዓላማ የዋለ መሆኑ ላይረጋገጥ ይችላል፡፡

2.11.3 **የማሻሻያ ሀሳብ፣**

የውስጥ ገቢ ሂሳብ በፋይናንስ ምንጭ የውስጥ ገቢ 1900 ተመዝግቦ ሪፖርት መደረግ ሲገባው የመደበኛ እና የውስጥ ገቢ ሂሳብ ሪፖርት በአንድ ላይ በ1800 ሪፖርት ከተደረገ ሂሳቡ ትክክለኛ ገፅታ እንዳያሳይ ከማድረጉም በተጨማሪ የ1800 የፋይናንስ ምንጭ የባንክ ሌጀር ከፍ እንዲል ያደረገና የ1900 የፋይናንስ ምንጭ የባንክ ሌጀር ዝቅ እንዲል ያደረገ በመሆኑም ለወደፊቱ ምዝገባ በሚከናወንበት ወቅት በፋይናንስ ምንጭ አመዘጋገብ ላይ ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.11.4 **የስራ አመራሩ ምላሽ፣**

ከዚህ በፊት በፋይናንስ ዳይሬክቶሬት የሰው ኃይል እጥረት በመኖሩ ምክንያት የተፈጠረና በኂላ እየተስተካከለ ያለ ሲሆን በያዝነው በጀት ዓመት 2010 ዓ.ም ሙሉ በሙሉ ችግሩ የሚቀረፍ መሆኑን እያሳወቅን በቀጣይነት ሁሉም ነገር ወደ መስመሩ የሚገባ ነው ብለዋል፡፡

3. **የተሰብሳቢ ሂሳብ፣**

3.1.1 **ግኝት፣ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ፣**

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32፣ የፌደራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ቅድሚያ ክፍያዎች በወቅቱ የሚወራረዱ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በሂሳብ መደብ 4203 ብር 2,560,208.51 ከአንድ ዓመት በላይ
- በሂሳብ መደብ 4211 ብር 19,788.63 ከሶስት ዓመት በላይ

- በሂሳብ መደብ 4253 ብር 75,511,457.97 ከአራት ዓመት በላይ የአቅራቢዎች ቅድመ ክፍያ ሲሆን ክትትል የማይደረግ መሆኑ
- በሂሳብ መደብ 4273 ብር 164,805.92 ከአንድ ዓመት በላይ፤

በጠቅላላ ብር 78,256,261.03 በደንቡ እና በመመሪያዉ መሠረት በወቅቱ ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡

3.1.2 ስጋት፤

ተሰብሳቢ ሂሳቦች በወቅቱ እንዲወራረዱ አለመደረጉ የመንግሥት ገንዘብ በወቅቱ እንዳይሰበሰብ ሊያደርግ ይችላል፡፡ በበጀት አጠቃቀም ላይም አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

3.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

በውዝፍ የሚታየው ተሰብሳቢ ሂሳብ በወቅቱ እንዲወራረድ እና የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር የኢንስቲትዩቱ ሥራ አመራር ተገቢውን ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

3.1.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፤

- 4203 በተመለከተ በተወሰኑ የተቋሙ ሠራተኞች የተወራረደ ቢኖርም ከ2008 ጀምሮ የተንከባለለ ተሰብሳቢ ሂሳብ ስላለ በቀጣይ በዚሁ በጀት ዓመት የማጣራት ሥራ ትኩረት ሰጥተን በመስራት በ2010 እርምጃ የምንወስድ መሆኑን እንገልጻለን፤

- 4211 በተመለከተ በወ/ሮ አረጋሽ ኩማ ስም የተያዘው ብር 16,121.88 ትኩረት ተሰጥቶ በሚቀጥሉት ወራቶች የሚወራረድ ነው፤

- 4253 በተመለከተ ከ2007 ዓ.ም. ጀምሮ ያለ ተሰብሳቢ ሂሳብ ወይም የአቅራቢዎች ቅድመ ክፍያ ስለሆነ የምዝገባ ችግር ስለሚኖር የማጥራት ስራ ተሠርቶ እርምጃ የሚወሰድበት መሆኑን፤

- 4273 በተመለከተ በ2008 ዓ.ም. መዋጮ ለማስተካከል በተሰብሳቢ የተያዘ ሂሳብን በ2010 በጀት ዓመት የማጥራት ሥራ ሰርተን የሚስተካክል መሆኑን ጭምር እንገለጻለን ብለዋል፡፡

3.2.1 ግኝት፤ ሂሳብ መደቡን ያልጠበቀ የተሰብሳቢ ሂሳብ፤

የተሰብሳቢ ሂሳቦች የሚያዙትና የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ግንቦት 1999 ዓ.ም በወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት በተገቢው የሒሳብ መደብ የሚመዘገቡ

መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ብር 15,119,420.00 የተሰብሳቢ ሂሳብ በተገቢው የሂሳብ መደብ ሳይመዘገብ ተገኝቷል፡፡

3.2.2 ስጋት፣

የፌዴራላዊ መንግስት የሂሳብ አወቃቃር ስርአት ተግባራዊ ካለመሆኑ በተጨማሪ የበጀት መዛበት ሊያስከትል ይችላል፡፡

3.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ

የተሰብሳቢ ሂሳብ ከመመዝገቡ በፊት የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ያወጣውን የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ተከትሎ በተገቢው የሂሳብ መደብ መያዛቸው መረጋገጥ ይገባዋል፡፡

3.2.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

ለወደፊቱ መመዝገብ ባለበት የሂሳብ መደብ ተገቢውን ማስተካከያ እንሰራለን ብለዋል፡፡

4. የተከፋይ ሂሳብ፣

4.1 ግኝት፣ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ፣

የተከፋይ ሂሳቦች ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ የተከፈሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- 5005 ልዩ ልዩ የደመወዝ ተከፋይ ሂሳብ ብር 115,420.61፣
- ኢንስቲትዮቱ በሂሳብ መደብ 5006 ብር 16,829.36 ዊዝ ሆልዲንግ ታክስ ለኢት/ገቢ/ጉምሩክ ባለስልጣን ያልተከፈለ መሆኑ፣
- 5028 ሌሎች ተከፋይ ሂሳብ ለመንግስት መ/ቤት ብር 134,765.00፣
- ኢንስቲትዮቱ በሂሳብ መደብ 5059 የቫት ክፍያ ሲሆን ብር 1,302,330.83 ለኢት/ገቢ/ጉምሩክ ባለስልጣን በወቅቱ ያልተከፈለ ሂሳብ

በድምሩ ብር 1,569,345.80 ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ ሳይከፈል መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡

4.2 ስጋት፣

የተከፋይ ሂሳብ ለባለመብቱ ድርጅት ለኢት/ገቢ/ጉምሩክ ባለስልጣን በወቅቱ ያልተከፈለና ለግለሰብ በወቅቱ አለመከፈሉ ገንዘቡ ለታቀደለት ዓላማ እንዳይውልና በበጀት አጠቃቀም ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

4.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ ለሚመለከተው አካል መከፈል ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ የማይሆን ከሆነ ግን የተከፋይ ሂሳቡ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

4.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

- 5005 ልዩ ልዩ የደመወዝ ተከፋዮች የድርጅት መዋጮ የሶሻል እና የገንዘብ ቁጠባ ከግለሰብ ደመወዝ የሚቀነስ እና የሚከፈል ሂሳብ መጠይቅ በቀረበበት ጊዜ ክፍያ የሚፈጸም መሆኑን እናሳውቃለን፣
- 5006 ዊዝ ሆልዲንግ ብር 16,829.36 በቀጣይ የማጣራት ሥራ ተሰርቶ የሚከፈል መሆኑን እንገልጻለን፣
- 5028 ለሌሎች ብር 134,765.00 የክፍያ ጥያቄ እንዲያቀርቡ በማድረግ ሲቀርብ የሚከፈል መሆኑን እንገልጻለን፡፡
- 5059 የቫት ተቀናሽ ተቆርጦ በመ/ቤታችን ክፍያ እንደሚፈጸም የሚታወስ ነው፡፡ በቀጣይ የማጣራት ሥራ ተሰርቶ ቀሪው ክፍያ ብር 1,302,330.83 የሚከፈል መሆኑን እንገልጻለን ብለዋል፡፡

5. <u>በጀት፣</u>

5.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>በስራ ላይ ያለዋለ እና ከበጀት በላይ የወጣ፣</u>

ኢንስቲትዩቱ በ2009 በጀት ዓመት የመደበኛ ወጪ በጀት አጠቃቀም በየሂሳብ ኮዶቹ ሲታይ ከ10% በላይ ብር150,576,883.00 ሥራ ላይ አልዋለም፡፡ በተጨማሪም ከበጀት በላይ ብር184,334,927.00 መሆኑ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

5.2 <u>ስጋት፣</u>

የወጪ ሂሣብ በጀቱ በዕቅዱ መሠረት አለመፈፀሙ ኢንስቲትዩቱ ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የበጀት ዕቅዱን ትክክለኛነት ላያመለክት ይችላል፡፡

5.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በበጀት ዕቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲሁም ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡እንዲሁም የበጀት እጥረት ሲያጋጥም ተጨማሪ የበጀት ጥያቄ ወይም ዝውውር ከሚመለከተው አካል መፈቀድ ይኖርበታል፡፡

5.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የበጀት ክፍና ዝቅ የማለቱ ጉዳይ የመጣበት ዋናው ችግር፣

1. በበጀት ዓመቱ በነበረው የሰው ኃይል እጥረት የተነሳ በጀት በአግባቡ መቆጣጠር ባለመቻሉ በተለይ ከመጋቢት 2009 ዓ.ም. በፊት ያሉ ወራቶች የበጀት ቁጥጥር ያልተደረገባቸው መሆኑ፣
2. የመጀመሪያው የሳተላይት ተቋማት በ2008 ዓ.ም. ግማሽ የጀመሩ በመሆናቸው ያልተወራረዱ ሰነዶችና ክፍያዎች በ2009 ዓ.ም. ግማሽ የጀመሩ በመሆናቸው ያልተወራረዱ ሰነዶችና ክፍያዎች በ2008 በጀት ዓመት ሊከፈሉ የሚገባቸው ክፍያዎች በ2009 ዓ.ም. በጀት ላይ ክፍያዎች በመከፈላቸው፣
3. ለተቋሙ ወጪ የሆኑና በ2008 በጀት ዓመት ሊከፈሉ የሚገባቸው ክፍያዎች በ2009 ዓ.ም. በጀት ላይ ክፍያዎች በመከፈላቸው፣
4. በተለይ ሳተላይት ተቋማት ከተመደበላቸው በጀት በላይ በመጠቀማቸው የተነሳና ሥራውም አዲስ ከመሆኑ የተነሳ ለተቋማቱ በተለያዩ ወቅቶች ጥሬ ገንዘብ በበላይ አመራሩ ውሣኔ አማካይነት የተላከ መሆኑ፣
5. በየዓመቱ ሲተላለፉ የመጡና ያልተወራረዱ የአውሮፕላን ትራንስፖርት፣ የውጪ ሃገር ጉዞ፣ የውጭ ሃገር ውሉ አበል ማስተካከያ የተሰራባቸው፣ ቅድመ ክፍያ የተከፈላቸው፣ የደንብ ልብስ የተገዛበት ለሳተላይት ተቋማት ነዳጅ የተከፈለበት ማስተካከያ የተሰራበት በተሰብሳቢ የተያዙ ሰነዶች በመኖራቸው፣
6. በበጀት ዓመቱ ከፌደራል ቴ/ሙ/ት/ሥ/ኢ ኤጀንሲ የተጨመረልን በጀት በመኖሩ (21 ሚሊዮን ብር) በበጀት ዓመቱ የውጪ ሃገር አሠልጣኞች ቅጥርና መሰል ጉዳዮች ከኤጀንሲ ወደ ተቋሙ በመምጣታቸው የተነሳ ብዙ ሥራዎች ከእቅድ ውጪ ሲሰሩ በመቆየታቸው እና ሌሎችም ሥራዎች ስለነበሩ መረጃው ከፋይናንስ ፒቪ እና ጀቪ ሙሉ ለሙሉ ተያይዟል፡፡ በማለት ገልፀዋል፡፡

6. <u>ንብረት፣</u>

6.1.1 <u>ግኝት፣</u> <u>የንብረት ገቢና ወጪ ደረሰኝ በሚመለከት፣</u>

የኢንስቲትዩቱ የንብረት አያያዝ፣ አጠባበቅና አመዘጋገብን ሁኔታ ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡በፌዴራል መንግሥት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት የስቶክ መዛግብቶች የመያዝና ስቶክ የመረከብ እንዲሁም ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶች ለአንድ ሰራተኛ መስጠት እንደሌለባቸው ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ የአላቂ ዕቃ እና የቋሚ ዕቃ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞዴል/19 እና የንብረት ወጪ ደረሰኝ ሞዴል/22

የሚዘጋጀውና የሚመዘገበው በአላቂ ዕቃ ግምጃ ቤት ሠራተኛ መሆኑ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

6.1.2 ስጋት፣

የንብረት አስተዳደሩ አሰራር መንግስት ባወጣው የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት የማይፈጸሙ ከሆነ ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

6.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ኢንስቲትዩቱ መንግሥት ባወጣው የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሠረት የንብረት አመዘጋገብ እና አያያዝ ሥርዓቱ እንዲስተካከል ተገቢውን ጥረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

6.1.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

ተቋሙ በንብረት አስተዳደር ስራ ክፍል ውስጥ በቂ ሰራተኛ ባለመኖሩ በተደጋጋሚ የንብረት ምዝገባ ሰራተኛ እንዲቀጠር የተጠየቀ ቢሆንም በገበያ ላይ ባለመገኘቱ የስራው አንቅስቃሴ እንዳይቋረጥ በሚል የንብረት ገቢና ወጪ በዕቃ ግምጃ ቤት ኃላፊ እንዲዘጋጅ የተደረገ ሲሆን በቀጣይ ለክፍሉ የሚያስፈልገውን ባለሙያ መድበን ስራውን በመነጣጠል የምናሰራ መሆኑን እንገልጻለን ብለዋል፡፡

6.2.1 ግኝት፣ ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ በሚመለከት፣

ኢንስቲትዩቱ በ2009 በጀት ዓመት መጨረሻ የቋሚ ዕቃዎች ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም በየቢሮው ለሚገኙት ቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር የተሰጠ እና የተቆጠረውም ዕቃ በስቶክ ካርድና በተጠቃሚዎች እጅ ላይ የሚገኙ ቋሚ ንብረቶች መቆጣጠሪያ ካርድ (User Card) ከተመለከተው ጋር የማመሳከርና የማስታረቅ ሥራ የተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት

- በመንግሥት ቋሚ ንብረት አስተዳደር ማንዋል (ጎፋም) መሰረት በተጠቃሚዎች እጅ ላይ የሚገኙ ቋሚ ንብረቶች መቆጣጠሪያ ካርድ (User Card) በሁለት ቅጅ ተዘጋጅቶ አንዱ ለተጠቃሚው ሌላው በንብረት ክፍል እንዲያዝ ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ የመ/ቤቱ ንብረት ክፍል የሚሰራበት አለመሆኑ፣
- የተቆጠሩት ቋሚ ዕቃዎች ከስቶክ ካርድና ከተጠቃሚዎች እጅ ላይ የሚገኙ ቋሚ ንብረቶች መቆጣጠሪያ ካርድ (User Card) ከተመለከተው ጋር የማስታረቅና የማመሳከር ሥራ ለመሰራቱ ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣

- ቋሚ ዕቃዎች በተሟላ ሁኔታ መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፣

በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

6.2.2 ስጋት፣

ኢንስቲትዩቱ በመንግሥት ቋሚ ንብረት አስተዳደር ማንዋል (ጎፋም) መሰረት የቋሚ ንብረት መለያ ቁጥር ያለመሰጠት እንዲሁም የቆጠራው ውጤት እንዲታወቅ ካልተደረገ የመንግሥት የሀብት አጠቃቀም፤ አጠባበቅና አያያዝ ሥርዓቱን ጥያቄ ውስጥ ሊያስገባው ይችላል፡፡

6.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የንብረት አስተዳደሩ መንግሥት ባወጣው የንብረት አጠቃቀም፤ አጠባበቅና አያያዝ መመሪያ መሠረት እንዲስተካከል እና እንዲፈጸም ኢንስቲትዩቱ ተገቢ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

6.2.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

ኢንስቲቲዩቱ ያለው የቋሚ ንብረት ምዝገባ ሠራተኛ አንድ በመሆኑና እሱም የሰራተኛ ፋይል ማደራጀት፣ User card መስራት፣ የገቢና ወጪ ካርድ ላይ መመዝገብ /ማቀናነስ/ ሲሆን ነገር ግን ካለው የስራ ጫና የተጠቀሰው ክፍተት ታይቷል፡፡ በቀጣይ አሰራሩን የምናስተካክል መሆኑን እንገለጻለን ብለዋል፡፡

6.3.1 ግኝት፣ ያልተወገዱ ንብረቶችን በተመለከተ

ኢንስቲትዩቱ በ2009 በጀት ዓመት የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ሲታይ የተለያዩ የመኪና ጎማዎች በቁጥር 20፣ ኮምፒዩተር ብዛት 7፣ ፕሪንተሮች ብዛት 4፣ ፎቶ ኮፒ ማሽኖች ብዛት 2፣ ፋክስ ማሽን ብዛት 1 እና የተለያዩ ቁርጥራጭ ብረታብረቶች አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች መኖራቸው በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

6.3.2 ስጋት፣

አሰራሩ በዚሁ ከቀጠለ የመንግሥት ንብረቶች ለብክነትና ለበለጠ ብልሽት ሊጋለጡ ይችላሉ፡፡ ለንብረት ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

6.3.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ኢንስቲትዩቱ የንብረት አስተዳደር መንግስት ባወጣው የንብረት አያያዝና አወጋገድ መመሪያ መሠረት አስፈላጊዉን እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

6.3.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የተጠቀሱት ዕቃዎች በተመለከተ ንብረት ክፍሉ በ2009 በጀት ዓመት አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች እንዲወገዱ ያደረገበት ሁኔታ አለ፡፡ ሆኖም እነዚህ ዕቃዎችም የተሰባሰቡት በ2010 በጀት ዓመት ለማስወገድ የተዘጋጁ መሆናቸውን ለማሳወቅ እንወዳለን ብለዋል፡፡

7. <u>ልዩ ልዩ፣</u>

7.1.1 <u>ግኝት፣ለየስራ ክፍሉ የስልክ ተመን አለመኖሩን በተመለከተ፣</u>

ኢንስቲትዮቱ ለሥራ አገልግሎት የሚውል የቀጥታ ስልክ መሰመር ለቁጥጥር እንዲያመች በየሥራ ክፍሉ የሚጠቀሙበት የስልክ ሂሳብ ተመን ያልተሰጠ መሆኑ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

7.1.2 <u>ስጋት፣</u>

- የኢንስቲትዮቱ የስልክ ሂሰብ ክፍያ ለኢንስቲትዮቱ ስራ አገልግሎት የዋለው ብቻ ላይሆን ይችላል፡፡
- የስልክ ሂሳብ ክፍያ አላግባብ ከፍ ብሎ ሊታይ ይችላል፡፡

7.1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ኢንስቲትዮቱ ለሥራ አገልግሎት የሚውል የቀጥታ ስልክ መሰመር በየክፍሉ የሚጠቀሙበትን የስልክ ሂሳብ ተመን በማውጣት ከተፈቀደላቸው በላይ የተጠቀሙ ሲሆን፣ ከሚመለከተው ሠራተኛ ተመላሽ የሚደረግበትን የቁጥጥር ሥርዓት ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

7.1.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የመደበኛ ስልክ አጠቃቀም በተመለከተ ስታንዳርድ ለማውጣት ከተለያዩ ተቋማት /ከደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ፣ ከትምህርት ሚኒስቴር፣ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እና ከአዳማ ዩኒቨርሲቲ) ልምድ በማሰባሰብ ስታንደርድ የተዘጋጀ ሲሆን በማኔጅመንት እንዲፀድቅ ቀርቧል ብለዋል፡፡

7.2.1 <u>ግኝት፣በቅጥርና በዕድገት ያልተሞሉ ክፍት የሥራ መደቦች፣</u>

ኢንስቲትዩቱ በዕቅድ የያዛቸውን ተግባራት በአግባቡ ለመፈጸም ይችል ዘንድ ክፍት የስራ መደቦችን በሰው ኃይል መሙላት እንዳለበት ይታመናል፡፡ ነገር ግን ኢንስቲትዩቱ ከተፈቀደለት

361 የስራ መደቦች ውስጥ በሰው ኃይል የተሞላው 157 ሲሆን 204 (56%) የሥራ መደቦች ክፍት መሆናቸው ታውቋል፡፡

7.2.2 <u>ስጋት፣</u>

የተሟላ የሰው ኃይል ባለመኖሩ ምክንያት ኢንስቲትዩት ዕቅዱን እንዳያሳካ ምክንያት ሊሆንና እንዲሁም በአሰራር ላይ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል፡፡

7.2.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ኢንስቲትዩቱ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ያስችለው ዘንድ ክፍት የሥራ መደቦችን በቅጥርና በእድገት እንዲሞሉ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

7.2.4 <u>የስራአመራሩ ምላሽ፣</u>

በኢንስቲትዩቱ ባለው መዋቅር የሞሉት የሰው ኃይል ብዛት 157 ሲሆን ቀሪ 204 የስራ መደቦች ያልተሞሉበት ምክንያት፣

- በበጀት ዓመቱ 17 ሠራተኞች ሥራ መልቀቅ፣
- በአንዳንድ የስራ መደብ ማለት በቧንቧ፣ ኤሌክትሪክሲቲ ግንበኛ እና ፀሐፊ በተፈቀደ መደብ ላይ እርከን ገባ ብለን ሠራተኛ አለማግኘት፣
- የICT የሥራ መደብ በቅርብ የተፈቀደና የሥራ ክፍሉ ገና ወደ ስራ እየገባ ስለሆነ በቀጣይ ማስታወቂያዎች በመውጣት የሰው ኃይሉን የማሟላት ስራ እንደምንሰራ በJEG ድልድል በኃላፊ የምናሟላ መሆኑ ከግንዛቤ ቢገባ ብለዋል፡፡

7.3.1 <u>ግኝት፣የሥጋት ተጋላጭነት ግምገማ (Risk Assessment) ያልተደረገ ስለመሆኑ፣</u>

የፌደራል መንግስት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 መሰረት የመንግስት መስሪያ ቤቶች የተቋቋሙበትን ዓላማዎች ለማስፈፀም ዕቅዶችና ዝርዝር የዕለት ተዕለት ተግባራት በማከናወን ሂደት የሚከሰቱ ችግሮችንና የተጋላጭነት ደረጃ ለመለየት የውስጥና የውጭ ኦዲተሮችንና ሌሎች የሚመለከታቸውን ባለሙያዎች በመጠቀም የስጋት ማንጮች ዳሰሳ ማካሄድ እንዳለባቸው ተመልክቷል፡፡ ሆኖም ኢንስቲትዩቱ የስጋት ምንጮች መለየት እና የስጋት ተጋላጭነት ፍተሻ ያላደረገ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

7.3.2 ስጋት፣

ኢንስቲትዩት የተቋቋመበትን ዓላማ ለማስፈፀም እንቅፋት የሆኑ ችግሮች በቅድሚያ ላይታወቁ ይችላሉ፡፡ ይህም ችግሮችን ለመቀነስ ሊሰራ የሚገባው ስራ እንዳይከናወን ሊያደርግ ይችላል፡፡

7.3.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ኢንስቲትዩቱ የሥጋት ተጋላጭነት ዳሰሳ ቢደረግ የዕለት ተዕለት ተግባራት በማከናወን በሂደት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ለይቶ ቅድመ ጥንቃቄ ለመውሰድ የሚኖረውን ጥቅም ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በተወሰነ ክፍል ብቻ ሳይሆን መ/ቤቱ በሚያከናውናቸው አጠቃላይ ተግባራት በመመሪያው መሰረት የስጋት ተጋላጭነት ዳሰሳ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

7.3.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

ኢንስቲቲዩቱ በአጠቃላይ ዕቅድ ክንውኖችንና የአሰራር ክፍተቶችን ለማስተካከል የሚመለከታቸውን አመራሮችና ባለሙያዎች በማሣተፍ 3 ዙር ሱፐርቪዥን በማካሄድ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን የስራ ክፍሎች ተለይቷል፡፡ በዚህ አግባብ እየሰራን ስለሆነ የውስጥ ኦዲትም በቀጣይ ዳሰሳ ጥናት እንዲያደርግ በተከታታይ የምናተጋው መሆኑን እንገልጻለን ብለዋል፡፡

7.4.1 የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ላይ ለተሰጠው የኦዲት አስተያየት እርምጃ አወሳሰድ፤

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ መግለጫዎችን እና የሂሳብ ሰነዶችን ኦዲት አድርጐ ሙያዊ አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳቦች ያቀረበ ሲሆን፣ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት ኢንስቲትዩት በግኝቶቹ ላይ እርምጃ የተወሰደ መሆኑ ሲጣራ፡- በተለያዩ የባንክ ወጪ ማስመስከሪያዎች እና የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣዎች በድምሩ ብር 3,168,870.89 የተከፈለው የወጪ ማስረጃዎች ያልቀረቡለት ሂሳብ መሆኑ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

7.4.2 ስጋት፣

ኢንስቲትዮቱ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የማስተካከያ እርምጃ የማይወሰድ ከሆነ፡

- ለኦዲት ሪፖርት የሚሰጠው ግምት አንስተኛ መሆኑን ሊያመለክት ይችላል፡፡
- የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም እንዲሁም ለመንግሥት ገንዘብ እና ንብረት መባከን እና አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

7.4.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ኢንስቲትዩቱ በኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጠው አስተያየት መሰረት አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ እንዳለበት በድጋሜ እናሳስባለን፡፡

7.4.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የምዝገባ ስህተት በSoft copy ያለውና በጄቪ ላይ የተመዘገበው የማይጣጣም በመሆኑ የተሰጠው የማሻሻያ ሃሣብ ሙሉ በሙሉ የምንቀበለውና ለወደፊት እንዳይደገም ትኩረት ሰጥተን የምንሰራው ይሆናል በማለት ገልፀዋል፡፡

በመጨረሻም ለተደረገልን መልካም የስራ ትብብር እናመሰግናለን !!